## መመሪያ ቁጥር፡ 1076/2017
## የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር የኢንተርንሽፕ መመሪያ

የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና ምርምር ተቋማት የኢንተርንሽፕ ፕሮግራምን በሁሉም የትምህርት መስኮች በሚጠበቀው ደረጃ እየተገበሩ ባለመሆኑ፤

ኢንዱስትሪዎች በኢንተርንሽፕ ዙሪያ ባላቸው የግንዛቤ እጥረት እና የዝግጁነት ውስንነት የተነሳ፣ እየጨመረ የመጣውን ኢንተርንሽፕ ፍላጎት እና ተደራሽነት ለማስተናገድ ተግዳሮት መሆኑ፤

ተገቢ የምደባ መስፈርት፣ የክትትል እና ግምገማ እንዲሁም ውጤታማ የተግባር ላይ ልምምድ ስርዓት በስራ ላይ ባለመዋሉ ፤

በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪዎች መካከል የተግባር ልምምድ ትግበራን ለማሻሻል በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ተሳትፎ እና አስተዋጽኦ ማጠናከር በማስፈለጉ፤

በመሆኑም ትምህርት ሚኒስቴር ከትስስር ምክር ቤት ጋር በመተባበር በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015 አንቀጽ 22 ንዑስ-አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## Directive No. 1076/2025
## Internship Directive for the Higher Education, Technical and Vocational Training, Research Institutions, and Industry Linkage

**WHEREAS,** higher education, technical and vocational training and research institutions are not implementing the internship program at the expected level in all fields of study;

**WHEREAS,** due to lack of awareness and preparedness of industries on internship, it became challenging to accommodate the increasing demand and accessibility;

**WHEREAS,** appropriate placement criteria, monitoring and evaluation system as well as well-defined method of internship is not implemented;

**WHEREAS,** with the need to strengthen the collaboration, engagement and contribution among higher education, technical and vocational training, research institutions and industries to improve the implementation of internships;

**THEREFORE**, the Ministry of Education, in collaboration with the Linkage Council, has issued this directive based on the provisions of the Higher Education, Technical and Vocational Training, Research Institutions, and Industry Linkage Proclamation No. 1298/2023, article 22 sub-article

## ክፍል 1

## ጠቅላላ ድንጋጌ

**አንቀጽ 1፡ አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **"የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር የኢንተርንሽፕ መመሪያ ቁጥር 1076/2017"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 2፡ ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **"ተለኪ ኢንተርንሽፕ"** ማለት ተማሪዎች በኢንዱስትሪ ውስጥ በመገኘት የተሻለ ዕውቀትና የሥራ ልምድ ባላቸው የኢንዱስትሪው ባለሙያዎች እና መምህራን ወይም በአሰልጣኞች አማካኝነት ክትትልና ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚለኩበት እና ውጤት የሚያገኙበት የተግባር ልምምድ የምዘና ሂደት ነው፤

2/ **"ተለኪ ያልሆነ ኢንተርንሽፕ"** ማለት ተማሪዎች በሚሰለጥኑበት የትምህርት ዘርፍ በተግባር የታገዘ ክህሎት እንዲጨብጡ በኢንዱስትሪዎች ውስጥ የተግባር ልምምድ የሚያገኙበት ፕሮግራም ሲሆን ለአካዳሚያዊ ትምህርት ውጤት አይውልም፤

3/ **"ኢንተርን"** ማለት በሰለጠነው የንድፈ-ሀሳብ የትምህርት ዘርፍ ላይ ተመርኩዞ የተግባር ልምምድ ለማግኘት በኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚሠራ ተማሪ ወይም ሰልጣኝ ማለት ነው፤

## Part 1

## General Provision

**Article 1: Short Title**

This directive may be cited as the **"Internship Directive for the Higher Education, Technical and Vocational Training, Research Institutions, and Industry Linkage No. 1076/2025".**

**Article 2: Definitions**

In this directive, unless the context otherwise requires:

1/ "**Graded Internship**" means an assessment process in which students receive results while being supervised and supported by industry professionals who have better knowledge and work experience in the industry and teachers of higher education institutions;

2/ "**Non-graded Internship**" refers to a program where students engage in practical internships in industries to gain relevant skills in their field of study, and it does not contribute to academic grading;

3/ **"Intern"** means a student or a trainee who works in industries to obtain practical experience based on the discipline of theory trained;

4/ **"የኢንዱስትሪ ባለሙያ"** ማለት ኢንተርኖችን እንዲያማክር እና እንዲያሰለጥን ኃላፊነት የተሰጠው በኢንዱስትሪ የሚመደብ ክትትልና ድጋፍ ለመስጠት የተሻለ እውቀትና ልምድ ያለው ባለሙያ ነው፤

4/ **"Industry personnel"** is an individual within an industry who has been assigned with the responsibility to supervise and train interns, possessing substantial knowledge and experience to provide oversight and support;

5/ **"የኢንተርንሽፕ ውል ስምምነት"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪው መካከል የሁሉንም ወገን ግዴታ እና የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመወሰን የተፈረመ ሰነድ ነው፤

5/ **"Internship Agreement"** is a document that is signed between a higher education, technical and vocational training, research institutions and the industry to define the duties, responsibilities and expectations of all parties;

6/ **"የስልጠና እቅድ"** ማለት በላኪውና በተቀባዩ ተቋማት መካከል የተግባር ልምምድ አሰጣጥን የሚመራ የድርጊት እና አፈጻጸም ዝርዝር ሰነድ ነው፤

6/ **"Training plan"** refers to a detailed document that guides the planning and delivery of internship between the sending and the industry;

7/ **"የኢንተርንሽፕ ገምጋሚ"** ማለት በላኪው ወይም በኢንዱስትሪው የሚገኝ፣ ኢንተርኖችን የሚያማክር፣ ስለ ኢንዱስትሪው ሁኔታ ገለጻ የሚያደርግ፣ የኢንተርኑን ስኬት እና ድክመት በተመለከተ ሪፖርት የሚሰጥ ባለሙያ ነው፤

7/ "**Internship Evaluator"** means a professional designated by either the sending institution or the industry to advise interns, provide industry context, facilitate the training, and report on the intern's performance, success, and challenges;

8/ በከፍተኛ ትምህርት፣ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015 አንቀጽ 2 ላይ የተሰጡ ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

8/ The definitions provided under article 2 of Linkage Proclamation No. 1298/2023 shall be applicable in this directive;

9/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

9/ In this directive, any term or provision that references the male gender shall also be inclusive of the female gender.

**አንቀጽ 3፡ የተፈፃሚነት ወሰን**

**Article 3: Scope of the directive**

ይህ መመሪያ በትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015 በተጠቀሱት በሁሉም የትስስር አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

This directive applies to all linkage actors mentioned in the Linkage Proclamation No. 1298/2023.

### አንቀጽ 4: የመመሪያው ዓላማ

በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትዎች መካከል የተግባር ልምምድ አግባብነት፣ ተደራሽነትንና ጥራትን ማሻሻል ነው።

## ክፍል 2

## የኢንተርንሽፕ ልምምድ አይነት እና የቆይታ ጊዜ

### አንቀጽ 5፡ ተለኪና ተለኪ-ያልሆነ ኢንተርንሽፕ

የተግባር ልምምድ እንደ ትምህርት መስክ አይነት ተለኪ እና ተለኪ-ያልሆነ በሚል በሁለት ዓይነት መንገድ የሚተገበር ይሆናል።

### 1/ ተለኪ ኢንተርንሽፕ

ሀ) ተለኪ ኢንተርንሽፕ አስገዳጅ የአካዳሚክ የተግባር ልምምድ ሲሆን ለመመረቂያ እንደ ቅድሚያ መስፈርት ሆኖ ያገለግላል፤

ለ) በተለኪ ኢንተርንሽፕ የኢንዱስትሪ ቆይታ ጊዜ ቢያንስ አንድ ሴሚስተር የሚኖረው ሲሆን በተለዩ የትምህርት ዘርፎች አስገዳጅ የተግባር ልምምድ ፕሮግራም እንዲኖራቸው ይደረጋል፤

ሐ) ኢንተርኖች በኢንዱስትሪው ውስጥ በሚያደርጉት ቆይታ በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል፤

መ/ በኢንተርንሽፕ ወቅት ተማሪዎች በኢንዱስትሪ ውስጥ በሳምንት 40 ሰዓት (በጠቅላላው ቢያንሰ 480 ሰዓታት) የተግባር ልምምድ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

### Article 4: Purpose of the directive

To improve access, quality and relevance of Internship among higher education, technical and vocational training, research institutes and industries.

## Part 2

## The Type and Duration of Internship Practice

### Article 5: Graded and Non- Graded Internship

Internship implementation can be applied in two ways, depending on the nature of the program as graded internship and non-graded internship.

### 1/ Graded Internship

a) Graded Internship is a mandatory internship allows academic assessment and serves as a graduation requirement;

b) Graded internship shall take at least one semester of industry experience and interns shall have mandatory internship programs;

c) Interns are supervised and supported by higher education, technical and vocational training, research institutes, and industry professionals during their stay;

d) The student must commit to work full-time based on a 40-hour per week (480 minimum total hours) during industry internship period.

## 2/ ተለኪ-ያልሆነ ኢንተርንሽፕ

ሀ) የተግባር ልምምዱ አስገዳጅ ያልሆነ፣ ውጤት የማይሰጠው እና ተማሪዎች ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለአጭር ጊዜ በመቆየት የሚቀስሙት የኢንዱስትሪ ውስጥ የተግባር ልምምድ ዓይነት ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጥ ይፋዊ የሆን ክትትልና ድጋፍ አይኖርም፤

ለ) ኢንተርኖችን የሚከታተለው እና የሚገመግመው የኢንዱስትሪው ባለሙያ ይሆናል፤

ሐ) አስገዳጅ ያልሆነ የኢንተርንሽፕ ፕሮግራም በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ከሃያ በመቶ ያላነሰ የተግባር ስልጠና ይሰጣል።

## ክፍል 3

## የኢንተርንሽፕ አስተዳደር

### አንቀጽ 6፡ የኢንተርንሽፕ ተደራሽነት፣ ምደባ እና ተገቢነት

1/ አንድ በኢንተርንሽፕ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ ተገቢነት ያለው ተማሪ/ሠልጣኝ በሁለተኛ ዓመት እና ከዚያ በላይ የትምህርት ጊዜ ላይ የሚገኝ እንዲሁም በተቋማቱ የተወሰነውን አነስተኛውን የክሬዲትሃወር ትምህርት የወሰደ መሆን አለበት፤

2/ የኢንተርንሽፕ ክሬዲትሃወር መጠን በትምህርቱ አይነት እና እንደ ተቋሙ ሁኔታ ከስምምነት ላይ የሚደረስበት ይሆናል፤

3/ በተቋማት እና በኢንዱስትሪ አማካኝነት የሚሰጠውን የኢንተርንሽፕ ፕሮግራም ገለጻ ያልወሰዱ ተማሪዎች በፕሮግራም ላይ መሳተፍ አይችሉም፤

## 2/ Non-Graded Internship

a) Non-graded Internship is a non-mandatory internship, in which a student gains industries' experience by working at an organization for a short period of time; there is no formal supervision from the higher education institution;

b) The industry professional shall follow and evaluate the intern;

c) Non-graded Internship shall be exercised in all field of studies to the minimum of 20% practical training.

## Part 3

## Governance of Internship

### Article 6: Access to internship placement and eligibility

1/ To be eligible for internship, a student must complete the minimum credit hours set by the higher educations, training and research institutions;

2/ Internship credit hours shall be agreed upon based on the type of the study and context of the sending institutions;

3/ Prospective interns who fail to attend an orientation organized by the higher education institutions and industries are not eligible to engage in internship;

4/ የተግባር ልምምድ በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና ምርምር ተቋም ውስጥ ባሉ ፕሮጀክቶች እና ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ሊሰጥ ይችላል።

4/ Internship can be offered in projects and enterprises within a higher education, technical and vocational training and research institution;

5/ ተማሪዎች ወደ ሌላ ኢንዱስትሪ በድጋሚ ሊመደቡ የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲከሰቱ ነው፡-

5/ Students may be reassigned to another industry only if the following situations happen:

ሀ) ከኢንዱስትሪው ጋር ተያያዥ በሆኑ ምክንያቶች ኢንተርኑ ውስጣዊ የተግባር ልምምድ ፕሮግራሙን መቀጠል ሳይችል ሲቀር፤

a) When the intern could not continue the internship due to industry-related causes;

ለ) ኢንዱስትሪው ኢንተርኑን ከሚማረው ትምህርት ጋር ተዛምጅነት በሌለው የስራ መደብ ላይ ሲያሰማራው፤

b) When the industry assigns the intern in non-appropriate position which is not aligned to his/her field of study;

ሐ) በስራ ላይ ልምምድ ፕሮግራሙ ላይ መሳተፍ የማይችል መሆኑ በህክምና ምርመራ ሲረጋገጥ።

c) Medical diagnosis recommends that s/he cannot continue in Internship.

6/ የኢንተርንሽፕ ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚወስን ዝርዝር መመሪያ በተቋማቱ ይዘጋጃል።

6/ Detailed guidelines will be prepared by the institutions to determine other administrative issues of internship.

**አንቀጽ 7፡ የኢንተርንሽፕ ቆይታ ጊዜ**

**Article 7: Duration of Internship**

1/ የኢንተርንሽፕ ፕሮግራም ግዴታ በሚሆንበት ጊዜ ቆይታው አንድ ሴሚስተር ማለትም እስከ አራት ወራት ድረስ ነው፤

1/ The mandatory internship lasts one semester, which is up to four months;

2/ ኢንተርኖች ከተግባር ልምምድ ቦታ ያለማስረጃ ለአምስት ቀናት ከቀሩ ይፋዊ ማስጠንቀቂያ የሚሰጣቸው ሲሆን ያለማስረጃ ለአሥር ቀናት ከቀሩ ከፕሮግራሙ ይሰናበታሉ፤

2/ Students being absent without proofs for more than five days during the internship period leads to final official warning and ten days’ absence without proofs lead to exclusion from the internship program;

3/ የኢንተርንሽፕ ፕሮግራም መርሃ ግብር የሚዘጋጀው በትምህርቱ የመጨረሻ ዓመታት በቀሪዎቹ ሦስት ሴሚስተሮች ውስጥ ይሆናል።

3/ In practice, the times of the internship shall be scheduled at the last three semester.

**አንቀጽ 8፡ የኢንተርንሽፕ የፋይናንስ ድጋፍ**

**Article 8: Internship Financing**

1/ ላኪ ተቋማት የጊዜውን የኑሮ ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት ወርሃዊ ቋሚ የኪስ ገንዘብ ሽፋን ያደርጋሉ፤

1/ Higher Education, Training and Research Institutions shall pay fixed amount of monthly amount which is mainly dedicated to cover their pocket money which is based on the current living cost;

2/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 የሚፈጸም ወርሃዊ ቋሚ የኪስ ገንዘብ ክፍያ በኢንተርኖቹ የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ይካተታል።

2/ In the same article sub-article 1 provides that the monthly fixed pocket fee shall be included in the cost sharing.

**አንቀጽ 9: ክትትል፣ ግምገማ እና ውጤት አሰጣጥ**

**Article 9: Supervision, Evaluation and Grading**

1/ እያንዳንዱ ተቋም በሚዘጋጀው በይነ-መረብ የተግባር ልምምድ መመዝገቢያ ቅጽ ላይ የሳምንት ተግባራቱን ማሳወቅ አለበት፤

1/ Each institution shall report weekly internship activities on the prepared online based internship registration platform;

2/ ላኪና ተቀባይ ተቋማት ለእያንዳንዱ ኢንተርን ከሚሰለጥንበት ሙያ ጋር ተዛማጅ ገምጋሚ ባለሙያ መመደብ አለበት፤

2/ Both the hosting and receiving institutions must assign a relevant evaluator with expertise related to each intern's field of study;

3/ እያንዳንዱ ገምጋሚ ኢንተርኑን ከተመደበበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ጊዜ በአካል እንዲሁም ስድስት ጊዜ በስልክ ወይም በኢሜይል ይከታተላል፤

3/ Each evaluator must monitor the intern at least twice in person and six times via phone or email throughout the internship period;

4/ የኢንዱስትሪው ገምጋሚ ኢንተርኑን በየቀኑ መከታተል ያለበት ሲሆን በተጨማሪም የበይነ-መረብ የተግባር ልምምድ መመዝገቢያ ቅጽ ቁጥጥር ማድረግ አለበት፤

4/ The industry internship program evaluator shall monitor the intern daily and follow-up the intern's online based internship registration platform;

5/ የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ገምጋሚዎች ለኢንተርኖቹ እንደ ቆይታ ጊዜያቸው በየወሩ መጨረሻ ቁጥጥር ያደርጋሉ፤

6/የኢንዱስትሪው ገምጋሚ የኢንተርኖችን የግምገማ ቅጽ ሞልቶ በሚስጥራዊ ሁኔታ ለከፍተኛ ትምህርት እና ለቴክኒክና ሙያ ስልጠናተቋም ማሳወቅ አለበት፤

7/ ኢንተርኑ ወርሃዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ለላኪው ተቋም እና ለኢንዱስትሪው ገምጋሚ ማቅረብ አለበት፤

8/ ኢንተርኑ የመጨረሻ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለገምጋሚ እና ለትምህርት ክፍል ማቅረብ አለበት።

**አንቀጽ 10፡ የኢንተርንሽፕ ውጤት አሰጣጥ**

የኢንተርንሽፕ ግምገማ ውጤት አሰጣጥ እንደሚከተለው ይሆናል:-

1/ በኢንዱስትሪው ገምጋሚ አርባ በመቶ፤

2/ የላኪው ተቋም ገምጋሚ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ እና የመጨረሻ ግምገማ ሪፖርት ሰላሳ በመቶ፤

3/ የስልጠና ቦታ አቴንዳንስ አሥር በመቶ፤

4/ በኢንተርኑ በቃል ለሚቀርብ ግምገማ ሃያ በመቶ ይይዛል።

**ክፍል 4**

5/ Evaluator in higher education and technical and vocational training institutions shall conduct monthly performance evaluations for their interns;

6/ The industry internship program evaluator shall complete the intern evaluation sheet and report to the higher education, technical and vocational training and research institutions in confidential manner;

7/ The intern must prepare a monthly report to submit to the hosting institution and the industry evaluator;

8/ The final report of the internship must be prepared and submitted to the evaluator and the department.

**Article 10: Internship evaluation grading**

The evaluation of the internship shall be as follows:-:

1/ Industry evaluator 40%;

2/ The sending institution's evaluator weekly, monthly, and final evaluation reports 30%;

3/ Attendance 10%;

4/ Evaluations of Intern’s oral presentation 20%.

**Part 4**

## የፈፃሚ አካላት ተግባር እና ሃላፊነት

## Roles and Responsibilities of Implementing Bodies

### አንቀጽ 11፡ የትምህርት ሚኒስቴር ተግባር እና ሃላፊነት

### Article 11: Roles and Responsibilities of Ministry of Education

የትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።

The Ministry shall have the following roles and responsibilities:

1/ ለመንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ፣ የግልና የማህበር ለሆኑ ድርጅቶች፤ ለከፍተኛ ትምህርት፣ ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት፣ ለምርምር ተቋማት እና ለማህበረሰቡ የተግባር ልምምድ ጠቀሜታን በተመለከተ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት እንዲከናወኑ ያስተባብራል፤

1/ Facilitate the creation of continuous awareness on internship for the private sector and the public organizations, the higher education, technical and vocational training and training and education institutions research institutions, and the community, the private sector and the public;

2/ የኢንተርንሽፕ ፕሮግራም ትግበራን በተመለከተ ህጋዊ ማዕቀፎችን ይቀርጻል፣ ያበለጽጋል፣ ትግበራውን ይደግፋል ይከታተላል፤

2/ Design and develop legal frameworks pertaining to the implementation of internship and support and monitor the implementation of internship programs;

3/ ዘላቂ የሆነ የኢንተርንሽፕ ፕሮግራምን ለማስፋፋት በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪዎች መካከል ሃገራዊ የውይይት መድረኮችን ያመቻቻል ይደግፋል፤

3/ Facilitate and support the national dialogue platform among higher education, technical and vocational training and research institutions and industries to promote and sustain internship;

4/ አጠቃላይ የኢንተርንሽፕ ትግበራን እና አመራርን ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

4/ Support, follow-up and monitor the overall implementation and management of internship;

5/ የኢንተርንሽፕ ፕሮግራም እንዲተገበር ድጋፍ ላበረከቱ ኢንዱስትሪዎች እውቅና እና የማበረታቻ ሽልማት እንዲሰጥ ለምክር ቤቱ ያቀርባል።

5/ Organize events to recognize and award best Industries that properly support the implementation of internship.

### አንቀጽ 12፡ የኢንተርን ተግባር እና ኃላፊነት

### Article 12: Roles and Responsibilities of Intern

ኢንተርኖች የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት

Interns have the following roles and

ይኖራቸዋል፡-

responsibilities

1/ ለኢንተርንሽፕ የሚወጡበትን ኢንዱስትሪ ከአንድ ወር በፊት አስቀድመው መለየትና ስለ ኢንዱስትሪው ለትምህርት ክፍላቸው ዝርዝር መረጃ ማቅረብ፤

1/ Secure appropriate internship placement one month in advance and inform the department about the details of the hosting industry;

2/ ተቋሙ በሚያዘጋጀው ገለጻ ላይ የመሳተፍ፤

2/ To participate in the orientation organized by the institutions;

3/ ከላኪውና ከተቀባዩ ተቋም ገምጋሚ ጋር በመተባበር በትምህርት ክፍሉ ተቀባይነት ያለው የኢንተርን የትምህርት ዕቅድ የማዘጋጀት፤

3/ Prepare the Student Learning Plan (SLP) in consultation with the Higher Education, Training and Research Institution and Industry evaluator which should be approved by the department;

4/ የተቀባዩን ተቋም ደንቦች፣ መመሪያዎችን እና የሥራ ሥነ-ምግባርን የማክበር፤

4/ Adhere to all the rules, regulations and standard requirements of the hosting Industry including punctuality, safety, working ethics;

5/ በተቀባዩ ተቋም ነባራዊ ችግሮች ላይ በመንተራስ ቢያንስ አንድ ፕሮጀክት ይቀርፃል፤

5/ Design a minimum of one project based on the existing problem of the Industry;

6/ የኢንተርንሽፕ ሪፖርትን አዘጋጅቶ ለትምህርት ክፍሉ እና ለተቀባዩ ተቋም ገምጋሚ ማቅረብ።

6/ Produce and submit internship report to the department and the Industry evaluator.

**አንቀጽ 13፡ የኢንዱስትሪ ተግባር እና ኃላፊነት**

**Article 13: Roles and Responsibilities of Industry**

ኢንዱስትሪዎች የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡-

Industries shall have the following roles and responsibilities :

1/ ለኢንተርኑ ተገቢውን ውስጣዊ የተግባር ልምምድ ምደባን ያከናውናል፤

1/ Secure appropriate internship placement for the intern;

2/ በኢንዱስትሪው ውስጥ ያላቸውን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ለአዳዲስ ኢንተርኖች ገለጻ

2/ Provide orientation to new interns before they start their operation in the industry;

ይሰጣል፤

3/ ከሙያው ጋር በቂ ልምድና ዕውቀት ያለው ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ ባለሙያ ይመድባል፤

3/ Assigning a qualified professional with adequate experience and knowledge to provide support and supervision;

4/ ለኢንተርኖች ስራቸውን የሚያከናውኑባቸውን ተገቢ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎችን፣ መገልገያ ዕቃዎችን፣ አቅርቦቶችን ያሟላል፤

4/ Provide an appropriate security equipment, appliances, supplies for the interns to engage in the internship;

5/ የኢንተርኑን የሥራ አፈጻጸም መከታተል እና መገምገም እንዲሁም ኢንተርኑ ከመጣበት ተቋም ሱፐርቫይዘሮች ጋር የመወያየት እና ግብረ-መልስ የመስጠት ሥራ ይሰራል፤

5/ Monitoring and evaluating the work performance of interns, and engaging in communication with supervisors from the organizations where the interns are placed to provide feedback;

6/ የኢንተርኑ ዝውውር ወይም የውል ስምምነት መቋረጥ አስፈላጊ ከሆነ ኢንተርኑን ለላከው ተቋም የኢንተርንሽፕ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት አስቀድሞ ያሳውቃል፤

6/ Notify the higher education, technical and vocational training and research institution internship coordination office in advance, if termination and transfer is necessary;

7/ የኢንተርኖችን የተግባር ልምምድ የሚያስተባበር ክፍል ያቋቁማል፤

7/ Establish a unit or section that facilitates the practical experience of interns;

8/ የኢንዱስትሪ ኢንተርንሽፕ ገምጋሚ ይመድባል፤

8/ Assign industry internships evaluators;

9/ የገምጋሚ ዝርዝር ተግባር እና ኃላፊነት ያዘጋጃል።

9/ Sets the detail duties and responsibilities of industry's' evaluator.

**አንቀጽ 14፡ የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና ምርምር ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት**

**Article 14: Roles and Responsibilities of Higher Education, Technical and Vocational Training, and Research Institutions**

1/ ተማሪዎች ወደ ሥራ ላይ ልምምድ ከመሰማራታቸው በፊት በቂ ገለጻ ይሰጣል፤

1/ Organize proper orientation for students before they engage in internship;

2/ ተማሪዎች ከሚያጠኗቸው የትምህርት ዘርፎች ጋር በተገናኘ በተገቢው ኢንዱስትሪ እና ትምህርት ዘርፍ መመደባቸውን ያረጋግጣል፤

2/ Ensure that interns are placed in appropriate industries in line with their fields of studies;

3/ ተቋማት፣ ኮሌጆች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ፋኩልቲዎች እና የትምህርት ክፍሎች የሥራ ላይ ልምምድን በአግባቡ መተግበራቸውን እና መምራታቸውን ያረጋግጣል፤

3/ Ensure that institutes, colleges, schools, faculties and departments properly implement and manage internship;

4/ ከኢንዱስትሪ ገምጋሚ ጋር በመተባበር ዓመታዊ የኢንተርንሽፕ ልምዶችን ይገመግማል፤

4/ Evaluate the yearly internship experiences in collaboration with the stakeholders, industries and evaluator;

5/ ለዓመቱ ምርጥ ኢንተርኖች እውቅና ይሰጣል፣ ይሸልማል፤

5/ Recognize and award best interns of the year;

6/ የተማሪዎችን የኢንተርንሽፕ ፕሮግራም የሚያስተባበር ክፍል ያቋቁማል፤

6/ They should establish a unit or department to coordinate the student internship program;

7/ የተቋሙን ኢንተርንሽፕ ገምጋሚ ይመድባል፤

7/ Assign institutional internships evaluators;

8/ የገምጋሚ ዝርዝር ተግባር እና ኃላፊነት ያዘጋጃል።

8/ Sets the duties and responsibilities of a list of evaluators.

## ክፍል 5

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## Part 5

## Miscellaneous Provisions

### አንቀጽ 15፡ ተፈጻሚ የማይሆኑ አሰራሮች

### Article 15፡ Non-Applicable Practice

ከዚህ በፊት በተለያዩ ስያሜ ይጠራ የነበረ የህግ፣ የጤና እና ሌሎች የተማሪዎች ወይም የሰልጣኞች የተግባር ስልጠና በዚህ የኢንተርንሽፕ መመሪያ እንዲካተት ተደርጓል።

Law, health, and other practical training programs that were previously referred to by various names have been incorporated into this internship directive.

**አንቀጽ 16: የመተባበር ግዴታ**

የትስስር አካል በሙሉ ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን የመተባበር ግዴታ አለበት።

**አንቀጽ 17: መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ትምህርት ሚኒስቴር ከትስስር ምክር ቤት ጋር በመተባበር ሊያሻሽል ይችላል።

**አንቀጽ 18: መመሪያው ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትምህርት ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ ግንቦት 21፣2017 ዓ/ም
ብርሃኑ ነጋ ቦንገር (ፕሮፌሰር)
የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር
ሚኒስትር እና የትስስር ምክር ቤት ሰብሳቢ

**Article 16: Obligation**

The linkage body has the obligation to ensure that this directive is effectively implemented.

**Article 17: Amendment of the directive**

This directive may be amended by the Ministry of Education in collaboration with the linkage Council, as necessary.

**Article 18: Effective Date of the directive**

This directive shall be effective as of the date registered by the Ministry of Justice and uploaded on the official website of the Ministry of Education.

**Addis Ababa, 29th May, 2025**
**Berhanu Nega Bonger (Professor)**
**Minister, FDRE, Ministry of Education and**
**Chair of Linkage Council**